
# የ Main Street ደኅንነት ማሻሻያ ፕሮጀክት

## የፕሮጀክቱ ወሰኖች




የፕሮጀክቱ ወሰኖች፦ ከ Massachusetts Avenue እስከ Portland Street

የ Cambridge ከተማ አስተዳደር በ Main Street ላይ የሚከተሉትን ለውጦች በማድረግ ላይ ነው፦

- በሁለቱም አቅጣጫዎች የተለዩ የብስክሌት መንገዶች ግንባታ
- ለእግረኞች የሚሆን የመሻገሪያ መንገዶች ማሻሻያ
- በ 50% እና ከዚያ በላይ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን መቀነስ
- መስቀለኛ መንገዶች ላይ ሊኖር የሚችለውን የደኅንነት ስጋት የማስወገድ ሥራ

## የፕሮጀክቱ መርሃ ግብር

*በፕሮጀክቱ እያንዳንዱ ምዕራፍ ላይ የማኅበረሰብ ስብሰባውን መሳተፍ፣ ኢንተርኔት ላይ አስተያየት መስጠት እንዲሁም የፕሮጀክቱን ሥራ አስኪያጅ ማግኘት ይችላሉ።*

**ምዕራፍ 1**
*መግቢያ*

የፕሮጀክቱ ዲዛይን አልነበረንም ነበር። ፕሮጀክቱን ለማኅበረሰቡ በማስተዋወቅ፣ አሁን ላይ ስላሉት ሁኔታችም አስተያየቶችን ተቀበለናል።

**ከማርች 2023 እስከ ሜይ 2023 መጨረሻ**

**ምዕራፍ 2 (አሁን ያለነው እዚህ ጋር ነው!)**
የዲዛይን አስተያየት

ጎዳናውን እንዴት እንደሚጠቀሙበት አስተያየት ሰምተን፣ ረቂቅ ዲዛይኖችን አውጥተናል። እነዚህን ዲዛይኖች አቅርበን አስተያየቶችን እየሰበሰብን ነው።

**ከጁን 2023 እስከ 2023 ማብቂያ ድረስ**

**ምዕራፍ 3**
አስተያየትዎ ተመራጭ ዲዛይን እንድናወጣ ይረዳናል።

እንድናወጣ ይረዳናል። ስለተሻሻለው ዲዛይን ያለዎትን አስተያየት ጠይቀን፣ በአስተያየትዎ መሰረት የመጨረሻዎቹን ለውጦች እናደርጋለን፣ እናም ፕሮጀክቱም እንዲፈጸም እንሠራለን።

**2024**

## የበለጠ ለማወቅ

www.cambridgema.gov/MainStreetSafety

የፕሮጀክቱ ድህረ-ገጽ፦

## የፕሮጀክቱን ሥራ አስኪያጅ ለማነጋገር

Stephen Meuse | smeuse@cambridgema.gov | 617-349-4713

የ Cambridge ከተማ ትራፊክ፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች፣ + የትራንስፖርት አገልግሎት


# የተለዩ የብስክሌት መንገዶች ምንድን ናቸው?





## የተለዩ የብስክሌት መንገዶች ምን ይመስላሉ?

- የብስክሌት መንገዶቹ ከመንገዱ ጠርዝ አጠገብ፣ ከእግረኛ መንገድ ጎን ይገኛሉ።
- የብስክሌት መንገዶች ከመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ጎን የሚገኙ ከሆነ፣ የብስክሌት መንገዶቹ በቆሙ መኪናዎች እና በመንገዱ ጠርዝ መካከል የሚገኙ ይሆናል።
  የብስክሌት መንገዶቹ ከመኪና ማቆሚያ ቦታዎች እና መጓጓዣ መንገዶች በነጭ ተጣጣፊ ምሰሶ ተለይተው ይገኛሉ።
- በመኪናዎች እና በስክሌት መንገዶች መካከል ተጨማሪ ክፍተት መኖሩ ሰዎች የመኪና በሮቻቸውን ብስክሌት ወደሚያሽከረክሩ ሰዎች አቅጣጫ እንዳይከፍቱ ይረዳል።
- ምሰሶዎቹ ሰዎች መኪናዎቻቸውን በብስክሌት መንገዶቹ ላይ እንዳያቆሙ ያደርጋሉ።



Softscape, the Noun Project


## የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን ማስወገድ የሚኖርብን ለምንድን ነው?

- የተለዩ የብስክሌት መንገዶች ከመደበኞቹ የብስክሌት መንገዶች ይሰፋሉ።
- ይህ የ Main Street ክፍል በሁለቱም አቅጣጫ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎችን ይዞ፣ የተለዩ የብስክሌት መንገዶችንም እንዲያካትት ለማድረግ በጣም ጠባብ ነው።

## Cambridge የተለዩ የብስክሌት መንገዶችን እየጨመረ ያለው ለምንድን ነው?

- በ Cambridge ውስጥ ሁሉም ሰው ብስክሌት እንዲያሽከረክር የሚያስችለው ደኅንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ የሆነ ሁኔታ እንዲኖር እንፈልጋለን። ይህን ለማድረግ እንዲያግዝ፣ አስፈላጊ የሆኑ መድረሻዎችን በብስክሌት መንገዶች እያገናኘን ነው።
- ብስክሌት የሚነዱ ሰዎች ያላቸውን የአደጋ ተጋላጭነት ለመቀነስ።
- መኪናዎች የሚያሽከረክሩበትን ፍጥነት ይቀንሳል፤ ይህም በበኩሉ ጎዳናው ለሁሉም ሰው ደኅንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ያደርጋል።

# የብስክሌት መንገድ ኔትዎርክ




**ቁልፍ፡-** ከጎዳና ውጪ ያሉ መንገዶች | የላቀ ልየታ | ዝቅተኛ መጠን እና ፍጥነት (ለብስክሌት ቅድሚያ የሚሰጥበት መንገድ)

ደኅንነቱ የተጠበቀ፣ ምቹ፣ የተገናኘ እና ሕዝብ ተኮር የሆነ የብስክሌት መንገድ <u>ኔትዎርክ</u> እየዘረጋን ነው። ይህ ብዙ ሰዎች ብስክሌት ማሽከርከር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።

## ለምን Main Street?

- ነዋሪዎችን እና ጎብኚዎችን ከመደብሮች፣ ሥራ ቦታዎች፣ መናፈሻዎች እና squares (አደባባዮች) ጋር ያገናኛል
- Kendall Square እና Central Square ያገናኛል
- ብስክሌት የሚያሽከረክሩ ሰዎችን ከሌሎች የተለዩ የብስክሌት መንገዶች ጋር ያገናኛል

## The Cycling Safety Ordinance

በ Cambridge City Council (Cambridge ከተማ ምክር ቤት) የተላለፈው Cycling Safety Ordinance (የብስክሌት ደኅንነት ድንጋጌ)፣ Cambridge 25 ማይል ገደማ የሚሆኑ የተለዩ የብስክሌት መንገዶች ግንባታን በኤፕሪል 2026 እንድታጠናቅቅ ያስችላታል።

ይህ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

- መላው Massachusetts Avenue
- Garden Street (ከምስራቅበኩል Huron Ave እስከ Berkeley St፣ በምእራብ በኩል ከ Mason St እስከ Huron Ave)
- Broadway (ከ Quincy St እስከ Hampshire St)
- Cambridge Street (ከ Oak St እስከ Second St)
- Hampshire Street (ከ Amory St እስከ Broadway)
- 11.6 ማይሎች በሌሎች ጎዳናዎች ላይ (በ Bicycle Network Vision (የብስክሌት መንገድ ኔትዎርክ ራዕይ) ውስጥ ከሚገኙት ውስጥ Main Street ጨምሮ)



በ Brattle Street ላይ የተለዩ የብስክሌት መንገድ

# Cambridge ውስጥ ያሉ መንገዶች ዲዛይን






## ዲዛይኑን በሁሉም የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎችን እና ብቃቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት እንሠራለን።

ጎዳናዎቻችን፣ የእግረኛ መንገዶቻችን እንዲሁም የብስክሌት መንገዶቻችን ከታች የተጠቀሱትን የማኅበረሰብ ክፍል በሙሉ ሊያገለግሉ ይገባል፦

### በሁሉም ዕድሜ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችን፦

- ሕፃናትን
- በዕድሜ የገፉ አዋቂዎችን

### የተለዩ መንቀሳቀሻ መሣሪያዎችን የሚጠቀሙ ሰዎችን፦

- መንቀሳቀሻ እስኩተሮችን
- የተላያዩ ብስክሌቶችን
- ዊልቸሮችን
- ተሽከርካሪ የሕፃናት ወንበሮችን
- የጭነት ብስክሌቶች
- እና ሌሎችም

### መኪና መገልገል የማይችሉ ሰዎችን፦

- ማሽከርከር ስለማችሉ ሊሆን ይችላል
- ማሽከርከር ስለማይፈልጉ ሊሆን ይችላል
- የማሽከርከር ወጪን መሸፈን ስለማይችሉ ሊሆን ይችላል

## መንገዶቹን ሰዎች እና ዕቃዎች በተደራጀ ሁኔታ እንዲቀሳቀሱ አድርገን ዲዛይን እናደርጋለን።

- የግል መኪናዎችን ከመጠቀም ይልቅ ብስክሌት ማሽከርከር እና የሕዝብ ትራንስፖርት መውሰድ፣ ውስን የሆነውን መንገድ በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል የተሻለ አማራጭ ነው።
  በወጣቶች እና በአዛውንቶች እንዲሁም በበርካታ ዓይነት ሰዎች ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የብስክሌት መንገዶችን ጨምሮ፣ ደኅንነታቸው ለተጠበቁ እና ተደራሽ ለሆኑ መገልገያዎች ዲዛይን እናደርጋለን።
- እንዴት ለትልቅ መኪናዎች እና በአካባቢው ለሚኖሩ ዴሊቨሪዎች መንገዶችን ደኅንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ ተደራሽ ማድረግ እንደምንችል እናስባለን።
- በጎዳናዎች ላይ ያሉ ክፍት የሕዝብ ቦታዎች እንደ ከቤት ውጪ መመገቢያ ወይም የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች በመሆን ሌሎች አገልግሎቶችንም መስጠት ይችላሉ።





ምስሎች፦ አውቶብስ ውስጥ፣ ብስክሌቶች ላይ እንዲሁም አንድ ሰው ብቻ በሚይዙ መኪናዎች ውስጥ በሚገኙ፣ ተመሳሳይ ብዛት ባላቸው ሰዎች የተያዘው መንገድ መጠን።

## ስለ መኪና መጨናነቅ እና መዘግየት ምን እናስባለን፦


ሰዎችን በዝግታ ማንቀሳቀስ፣ የሰዎችን ደኅንነት መጠበቅ ነው።

- የሚያሽከረክሩ ሰዎች እንዳይዘገዩ ከማድረግ ይልቅ የመንገዶቻችንን ደኅንነት መጠበቁ ይበልጥ አስፈላጊ ነው።


# የ Main Street ደኅንነት ማሻሻያ ፕሮጀክት

## የዲዛይን አማራጮች:- ከ Sidney Street ኤክስቴንሽን እስከ Windsor Street

<u>አማራጭ 1:- የመኪና ማቆም የሚፈቀደው በሰሜን በኩል ብቻ ነው</u> (9 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች)




<u>አማራጭ 2:- የመኪና ማቆሚያ ቦታው Cherry Street ላይ አቅጣጫ ይቀይራል</u> (13 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች)




## የመኪና ማቆሚያ ቦታ ለውጦች

| | አሁን | አማራጭ 1 | አማራጭ 2 |
|---|---|---|---|
| **ጠቅላላ ቦታዎች** | **26** | **9** | **13** |
| *ፍቃድ* | *0* | *ውሳኔ ይሰጥባቸዋል* | *ውሳኔ ይሰጥባቸዋል* |
| *በመጫን ላይ* | *2* | *ውሳኔ ይሰጥባቸዋል* | *ውሳኔ ይሰጥባቸዋል* |
| *ሜትር* | *23* | *ውሳኔ ይሰጥባቸዋል* | *ውሳኔ ይሰጥባቸዋል* |
| *ተደራሽ* | *1* | *1* | *1* |

*መኪና ማቆሚያ ቦታው በየትኛው የመንገዱ ክፍል መሆን አለበት?*

*እዚህ ምን ዓይነት የመኪና ማቆሚያ/ሎዲንግ ቦታ ነው የሚያስፈልገው?*

*ይበልጥ አስፈላጊ የሆነው የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ብዛት ነው ወይስ የሚገኙበት አካባቢ?*

## የትኛውን ይመርጣሉ? ከታች አንድ እስቲከር ያስቀምጡ

አማራጭ 1:-
መኪና ማቆሚያ ቦታዎች በሰሜን በኩል ብቻ ይሆናሉ (9 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች)

አማራጭ 2:-
መኪና ማቆሚያ ቦታው አቅጣጫውን ይቀይራል (13 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች)

ከላይ የተጠቀሱ ጉዳዮች የዳሰሳ ጥናትንም በኦንላይን ማግኘት ይቻላል:- camb.ma/mainstreetsurvey


የ Cambridge ከተማ
ትራፊክ፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች፣ +
የትራንስፖርት አገልግሎት

የፕሮጀክቱ ድህረ-ገጽ:-


# የ Main Street ደኅንነት ማሻሻያ ፕሮጀክት

## የዲዛይን አማራጮች፡- ከ Windsor Street እስከ Portland Street


አማራጭ 1፡- የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በሰሜን በኩል ብቻ ይሆናሉ (19 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች)




አማራጭ 2፡- የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በደቡብ በኩል ብቻ ይሆናሉ (29 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች)




አማራጭ 3፡- የመኪና ማቆሚያ ቦታው በ Osborn Street ላይ አቅጣጫውን ይቀይራል (22 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች)




## የመኪና ማቆሚያ ቦታ ለውጦች

| | አሁን | አማራጭ 1 | አማራጭ 2 | አማራጭ 3 |
|---|---|---|---|---|
| **ጠቅላላ ቦታዎች** | **50** | **19** | **29** | **22** |
| *ፍቃድ* | *32* | *19* | *29* | *22* |
| *በመጫን ላይ* | *1* | *0* | *0* | *0* |
| *ሜትር* | *27* | *0* | *0* | *0* |

የማኅበረሰቡ አባላት እዚህ አካባቢ ላይ የሚገኙት የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች በሙሉ permit parking (መኪና የማቆም ፈቃድ) ሊጠየቅባቸው ይገባል ብለውናል።

በጣም አስፈላጊ የሆነውን ያስቡ፡-
- አጠቃላይ የማቆሚያ ቦታዎች ብዛት
- ማቆሚያ ቦታዎች ቤቶች ባሉበት ተመሳሳይ አቅጣጫ ላይ መሆናቸው
- የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች ዲዛይን/አቀማመጥ

## የትኛውን ይመርጣሉ? ከታች አንድ እስቲከር ያስቀምጡ

| አማራጭ 1፡-<br>መኪና ማቆሚያ ቦታዎች በሰሜን በኩል ብቻ ይሆናሉ<br>(19 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች) | አማራጭ 2፡-<br>መኪና ማቆሚያ ቦታዎች በደቡብ አቅጣጫ ብቻ ይሆናሉ<br>(29 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች) | አማራጭ 3፡-<br>የመኪና ማቆሚያ ቦታው አቅጣጫውን ይቀየራል<br>(22 የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች) |
|---|---|---|

ከላይ የተጠቀሱ ጉዳዮች የዳሰሳ ጥናትንም በኦንላይን ማግኘት ይቻላል፡- camb.ma/mainstreetsurvey

የ Cambridge ከተማ
ትራፊክ፣ የመኪና ማቆሚያ ቦታዎች፣ +
የትራንስፖርት አገልግሎት

የፕሮጀክቱ ድህረ-ገጽ፡-